# "ሰይጣን ሲያርም ባህታዊ ያስንቃል"

(ከህያዉ ቃል )

"ጊዜ የምንማርበት ት/ቤት ፤የምንነድበትም እሳት ነዉ።"

(ዴልሞር ሽዋርትዝ)

ተማርንበትም ነደድንበትም "ጊዜ ዳኛዉ" በህልፈቱ "የማያልፍ ስም" እየሰጠን እንደዘበት ይነጉዳል ። ይኸዉ ፤ ከረጅሙ የሀገራችን ዕድሜ አንጻር ሲለኩ ኢምንት የሚመስሉ ሁለት አሰርት ዓመታት ከዐይኖቻችን ሥር ተፈተለኩ ። እነዚህ ዓመታት በኢትዮጵያ ሕልዉናና በሕዝቧ ሕይወት ላይ የራሳቸዉን አሻራ አስቀርተዉ ያለፉ ምስቅልቅልና ዉጥንቅጥ የበዛባቸዉ ሁኔታዎችን አስመዝግበዉ አልፈዋል ። ከነዚሁ ዉስጥ መኻንነቱ በሕዝብ ዘንድ በሚታመንበት ወርሀ ግንቦት የተከሰተዉና የሀገራችንን ግዛታዊ ክልል ሳይቀር ያኮሰመነዉ "ለዉጥ" ዐቢዩን ቦታ ይወስዳል ።

ከሃያ ዓመታት ጥቂት ዘለቅ በሚለዉ በዚህ የዘመን ማዕቀፍ ዉስጥ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ በዐረመኔአዊ ጭካኔዉ ሲጠቀስ የሚኖር አንድ ግፈኛ ወታደራዊ አገዛዝ በአፍጢሙ ሊደፋ በቅቷል ። ያ ወቅት ግን ሁኔታውን በአጸደ ሕይወት ቆመዉ ለመመልከት ባልታደሉቱ አያሌ አንጡራ የሕዝብ ልጆች መስዋዕት ለዕዉንነት የመብቃቱን ያህል በትግላቸዉ የተመኙለትን "የድል ፍሬ" ለማዘል ሳይታደል ቀረ ። ይሁንና ፍጅትንና ስዬልን የዘመነ ስልጣኑ መለዮ አድርጎ አስራ ሰባት ዓመታት የከረመዉ "ልበ ደንጊያ" ኮሎኔል በትዉልድ ደም በጨቀዬ ዜና ሕይወቱ ላይ "ማፈርያና ወራዳ" ምግባርን ደርቦ በማሸረጥ ከሀገሩ ምድር ፈረጠጠ ። ይህ እዉነታ ከእንግዲሁ (አሳፈረም አላሳፈረ ) የታሪካችን አንድ ገጽታ ሆኖ ሰፍሯል ። መንግስቱና ጨካኝ ሎሌዎቹ በዐምሮት ተቃጥለዉ ፍግም ይሏታል እንጂ ከንግዲህ ወድያ ዐረመኔዉ አምባገነን ዳግም ላይመለስ ከፖለቲካዉ መድረክ ተሽቀንጥሯል። በርሱ ፈንታ የርሱ ዉጤት የሆነ፤ የርሱዉ ቢጤ ቀኑን ጠባቂ ፤ ሌላ የቀን ጅብ ከስልጣኑ ወንበር ላይ ተፈናጥጧል ። ሀገራችንና ሕዝቧ በዕዉን የደረሳቸዉ ዕጣ ከከፉ ቅዠት የሚመደብና በአያድርስ የሚያስደነብር ክስተት ነዉ ።

ያ ሰዉዬ ፤ የያዘዉን ይዞ-ያሻዉንም አስጭኖ ፤ ዘረኛ አሳዳጆቹን መመከት ይቅር ፤ ለማስመሰል ያህል እንኳ "እንገፍ እንገፍ" ሳይል ነበር የተፈተለከዉ ። በፍርሐት ረጥቦ ዝምባብዌ ላይ ሲከትም ምትክ አሳዳጆቹ ይቅርና አዲስ አበባን ሊይዙ ገና ወደ ሰሜን ሸዋ ዘልቀዉ መተኮስ አልጀመሩም ።የተፈጥሮ ፍርሀቱን በጭካኔዉ ለምድ ስር ደብቆ የከረመዉ ይህ ቡከን ኮሎኔል "የጦር ሀይሎች ጠቅላይ አዛዥ" የተሰኘዉን ታላቅ ወታደራዊ ማዕረግ በመናኛ ሰዉነቱ ላይ ደራርቦ የተሸከመ "ጄኔራልም" ነበር ። ይህም ብቻ አይደለ ፤ ለነዉሩ ማባሪያ የሌለዉ ይህ ሰዉ ፤ በወቅቱ ሰሜናዊቷን ኢትዮጵያዊ ግዛት ከግንጠላ ለማዳን በመደረግ ላይ በነበረዉ ፍልሚያ ገንጣዮቹን ሀይሎች ገትረዉ የያዙለትን ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንኖች በ "ሀገር ክህደት" ከስሶ ከሚመኑት ጦር ፊት

አቁሟል ። ያም ብቻ አይደለ ፤ ራሱ የጫነላቸዉን ማዕረግ ከትከሻቸዉ ላይ በመቀስ እየቀነጠሰና "....ቂጣቸዉን በሳንጃ እየወጋ ..." አዋርዷቸዋል ። አስረሽኗቸዋልም ። ዛሬ ዛሬ ኢትዮጵያ ለተጥለቀለቀችበት የዉርደት ጎርፍ የመጀመሪያ ረድፍ ተጠያቂነቱ ከራሱ ሊወርድ ከቶ አይችልም ።

ለዚህ ምክንያቱ በወቅቱ በደም ፍላት የወሰደዉ "አብዮታዊ ርምጃ" እኒያ በዉጊያ ልምድ የበለጸጉ የጦር መኮንኖች ዘረኞቹን ተዋጊዎች ጎትተዉ ያቆዩበትን ክትር በመንደልና በመደርመስ ሀገር የምትጠቃበትን በር ከፍቶ ያሳደረ በመሆኑ ነዉ ። ይህ ብቻዉን ኮብላዩን "ጀኔራል" በሀገር ክህደት ወንጀል ከጦር ፍርድ ቤት ሊገትረዉ የሚችል ወንጀል ለመሆን በበቃ ነበር ።

"የጉድ አገር ኝንፎ እያደር ይፋጃል" እንዲሉ ሆነና ፤ ይህ ከታሪክ ማማና ሰገነት ላይ በነዉረኛ ምግባሩ የተከሰከሰ ዉዳቂ ዳግም በህይወት ላይ አስፈሪ ጥላዉን ሊያጠላ "በታሪክ ዘጋቢነት" ብቅ ማለቱ ሰሞነኛዉ መነጋገርያችን ሊሆን በቅቷል ። የአንድ ሚሊዮን ዶላር ክፍያ ለማግኘት ገበያ ሲያፍላልግ መቆየቱም ተዘግቧል ። ጥረቱ ይስመር ወይ አይስመር አይታወቅም ። አሳታሚ አግኝቶ "ደራሲ" የመባሉ ጉዳይ ግን አገር ያወቀዉ ጸሀይ የሞቀዉ እዉነት ሆኖ ከርሟል ። ...ኮብላዩ የጦር ወንጀለኛ በአንፋሽ አጎንባሾቹ ዘንድ..."ደራሲ መንግስቱ ኃይለማርያም ፡ የኢሰፓ ሊ/መ ፤ የሸንጎዉ ሰባሳቢና የጦር ሀይሎች ጠቅላይ አዛዥ ..." እየተባለ መጠራት ጀምሯል ። ሰዉዬዉ ስሙን ለማተለቅ ሲደረድራቸዉ ከነበረዉ የስያሜ ጋጋታዎች አንጻር አዲሱ መጠሪያዉ አይከብደዉ ይሆናል ። ነገር ግን "ሹመት ያዳብር" በሚል ማዳነቂያ ይህን የሰዉ ጭራቅ ማሞገሱ ሌላዉ ቢቀር በታሪካችን ሂደት አንድ ወቅት ላይ የኢትዮጵያንና የሕዝቧን መጻዒ ዕድል የተቃና ለማድረግ በመንቀሳቀሳቸዉ ሰለባዉ ላደረጋቸዉ ፤ በጎዶሎ አካል እስከዛሬ ለከረሙት ፤ ወይም ከጅምላ መቃብር ኖራ በለወሷቸዉ ሰማዕት ጀግኖቻችን ማፌዝ ይሆናል።

ወንጀለኛዉ ኮሎኔል ይቅርና በታሪክ ዘጋቢ-ደራሲነት መሞካሸት በተደላደለ ኑሮና በሙሉ አካል ከህግ ተሰዉሮ መሰንበቱ በራሱ ትልቁ የታሪካችን አንድ ስህተት ነዉ ። የአቅማችን ዉስንነትም ዉጤት ነዉ ። እንጂ በሩዋንዳ ዕልቂት በንክኪ የተጠረጠሩ ጥቃቅኖቹ ሹመኞችና የኮትዲቯሩ ላዉረንት ግባግቦ የትና እንደምን እንደሚገኙ የሚታወቅ ጉዳይ ነዉ ። ግፈኞች በሕጋዊ አሰራር የእጃቸዉን እንዲያገኙ መደረጋቸዉ በምንም ዓይነት መልኩ ከበቀል የሚቆጠር ጉዳይ አይደለም ።

ሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት ከተጠናቀቀ ስድሳ ስድስት ዓመታት ተቆጥረዋል ። በደቡብ አሜሪካ አገሮች ተደብቀዉ የነበሩ የናዚ ወንጀለኞች እንደምን እስከዛሬ እንደሚታደኑ ልብ ልንል ይገባል ። በጊዜ ብዛት በርጅና መሞታቸዉ ከታወቀ በኋላ እንኳ መቃብራቸዉ ተፈንቅሎ አጽሙ በርግጥ የተፈላጊዎቹ ወንጀለኞች መሆን አለመሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ ነዉ የምርመራ መዝገባቸዉ የሚዘጋዉ ። አቅማችን የሞሳድን ያህል ባለመደርጀቱ እንዘን እንጂ ከሔይንሪክ ሂምለርና ከሔንሪክ ሙለር የማይተናነሱ የራሳችን ሰዉ በላዎች ሞልተዉናል ። አሁን ማን ይሙት የ"ማዴቦ ገዳዮች ቡድን" ከጀስታፖ ይተንሳልን? በየደረሱበት የመግደል ፈቃድ የነበራቸዉ አሊ ሙሳን የመሳሰሉ አረመኔዎችስ የመተርሯቸዉና ግፍን ለመፈጸም በነበራቸዉ ጥድፍያ ሳቢያ ከነነፍሳቸዉ አፈር ያለበሷቸዉ ኢትዮጵያዉያን ብዛታቸዉ ይታወቃልን ?...ለመሆኑ የግፈኞችን ጉዳይ ጠቅልለን ለበቀል አምላክ መተዉ ይኖርብናልን ?...ወይስ ከየጫንቃዎቻቸዉ የሚጎተተዉ የግፍ ዛዝላ እያንዳዳቸዉን ሐይቅ ዉስጥ አስጥሞ እንደ ጌታቸዉ ሽበሺ እስኪገድላቸዉ እንጠብቅ ?

ለመጭዎቹ ዘመናት ታሪካችን የምናስብ ከሆነ የሀላፊዎቹን ዘመናት ግፈኞች እያንጠለጠለ የሰከነ ፍትሕን ከሚያነጥር ሕግ ፊት የሚያቀርብ ተቋም ሊኖረን ይገባል ። እንጂማ ደራሲ ተብዬዉን ወንጀለኛ ቀድመዉትም ሆነ ተከትለዉት ከሀገር የኮበለሉ አባሪ ተባባሪዎቹ ዬት ዬት እንደሚኖሩ ይታወቃል ፤ ሀገር ቤት ቀርተዉ ወያኔን የሚካድሙትንም እንደዚያዉ ። ዐይን አዉጣዎቹማ የአባት ስም በለወጡ ብቻ የተዘነጉ መስሏቸዉ በአዲሶቹ "ስልጡን" የፖለቲካ ድርጅቶች ዉስጥ የስራ አስፈጻሚ ወንበር ይዘዉ በዉስጠ ወይራ "ማዴቦ አባታችን ለዘለዓለም ይኑር" እያሉን ነዉ ። ይህን ያስተዋለ ስለመጭዉ ዘመን ስጋት ቢገባዉ ይፈረድበታልን ?…ግፍስ ምን ያህል ቢቀል ነዉ የሰዉ ነፍስ-ስጋ በጥሬዉ ከመብላት ያልተመለሱ ወንጀለኞች ጉዳይ ሲነሳ የፍትህ ጥያቄአችን በደል የሚሆነዉ?

በኮሎኔል መንግስቱና "ትግላቸዉ" ሕትመትና ስርጭት  ክንዉን ዉስጥ ብዙዎች ተንቦጫርቀዉበታል ። ሰዉ እንደየእድሩ ይሰለፋልና ዛሬም ጥቂቶች በመንቦራጨቁ ገፍተዉበታል ። በኔ ዕይታ ከመስመር ወጣ ብሎ ያለዕድሩ ገብቶ (ምናልባትም በየዋህነት) የሚታየዉ  ትንሹ ኤልያስ ብቻ ነዉ ፤አሳታሚዉ ። "በሬ ሆይ …በሬ ሆይ ….." ብለዉ ሊተርቱበት የሚቃጣቸዉ ቢኖሩ የዘመኑ የወረት ስልት ያልገባቸዉ  መሆን ይኖርባቸዋል ።

በአለንበት የንግድና የቢዝነስ ጥድፍያ ዘመን አንድን ነጋዴ በደም ንግድ ለመክበር ከሚደረግ ሩጫ ሊያቅበዉ የሚችል ሁነኛ መግቻ  ቢኖር በግሉ ያለዉ ሞራላዊ አቋም ብቻ ነዉ ። በዚህ ዘመን ፤ በዚህ ዓለም ገንዘብ እስካስታቀፈ ድረስ በግልጽም ሆነ በድብቅ የማይሸጥ የማይቸበቸብ ነገር ያለ አይመስልም ። አደንዛዥ ዕጽ ፤ የጦር መሳርያዎች ፤ የሰዉ አካል ብልቶች ፤ … ወዘተ ተሸቅጠዉ ሆጭ ካለ የገንዘብ ቁልል አናት ላይ በአንድ አፍታ ሲያስቀምጡ ይታያል ። በዚህ መሰሉ ህብረተሰብ ዉስጥ ራሱን ላገኘ አንድ ስደተኛ ትርፍ አላሚ ደግሞ ፤ በታሪክ ስም ከተጠረዘ "የደም መጽሐፍ" ትርፍን ማጋበስ በአዲሱ አማርኛ -"አሸወይና" ፤ ወይም ወደ ከበርቴነቱ አምባ ቀላሉ ማሳለጫ ስራ መስሎ ሊታይ መቻሉ አያጠራጥርም ።

"የደም አልማዝ" ፤ " የደም ገንዘብ" ….ወዘተ የተሰኙትን ወንጀል ነክ ሐረጎች እስከነመኖራቸዉ እንኳ የማገናዘቡ ጉዳይ ደግሞ ትርፍን ከማለም ርቆ የሚያስኬድ የአዕምሮ ባለቤትነትን የግድ ይላል ።ከሰዎች ቆዳ በዕዉቅ የሚሰፋ ጫማ አትራፊ ሆኖ ቢገኝና ዳጎስ ያለ ገንዘብ ወደ ካዝና ሊያስገባ እስከቻለ ለአንዳንዱ ነጋዴ ሞራላዊ ዕዳዉ ከገብስ ቀልሎ ቢታይ ምን ይባላል?… ፍርድ እንደራስ ነዉ ። ቀድሞ ነገር "በብሔራዊ  ደረጃ የተሰራ ወንጀል" ክብደቱ ብሔራዊነት በወጉ ለሰረጸበት ህሊናም አይደል? … ሰብዐዊነት ላይ የተፈጸሙ ጥፋቶችም ማንገብገባቸዉ የሰብዐዊነታችንን ያህል ነዉ። …" ከሌለህ የለህም" ነዉ የሚል ዘፈኑ ?…ለትንሹ ኤልያስ አዘንኩለት ። አዉቆም ሆነ ተሳስቶ ከገባበት ማጥ አንዳች መዉጫ ከወዲሁ ካላበጀለት ኪሳራዉን ገና ገና አልጀመረዉም ። አጭሩን እንዲያደርግለት ምኞቴ ነዉ ።

ሌላዉ ተንቦጫራቂና የ"መጽሐፉ" ጠበቃ ደግሞ በደብረ ዘይት "ልጅነቱ" በመማል መርዝ ነስንሶ ሚደጉሳቸዉን "ድርሳነ ምስጢራት ወወያኔ" ቸብቸቦ እብስ የሚለዉ  ጓደኛ ነዉ ። የዚህን ሰዉ ነገረ ስራ ሳስተዉል የተረትና ምሳሌይቱ የሌት ወፍ ትታሰበኛለች ። ይህቺ ፍጡር ቀን ቀን አይጦች ሰፈር ትደበቅና "አይጥ ነኝ" ስትል ስታዉራ ትዉላለች ። ሌቱን ደግሞ ወደ ወፎች መኖሪያ ትዘልቅና "ዘራፍ እኔ ወፊቱ"ን ታዜማለች ። በዚሁ ብልጠትዋ የተነሳ ወፍነቷ ወይም አይጥነቷ ተለይቶ ባለመታወቁ  እስከዛሬም ታምታታበታለች ። የደብረ ዘይቱ የሌት ወፍም እንዲሁ አይወርደዉ ሽጥ አያቋርጠዉ ድንበር የለዉም ። አስመራ ከርሞ የተሰጠዉን የቤት ሥራ

በኮሮጀዉ አንጠልጥሎ ይመለስና ፤ ከኔም በላይ "ስለኢትዮጵያ የሚያዉቅ - ለኦሮሞ የሚጨነቅ ለአሳር ነዉ" ሲለን ይሰነብታል ። የሌት ወፍ መሰሉ ሰዉ የአያሌ ሰማዕት ጀግኖቻችንን ገድል እያሳተመና በእፎይታ የሱቅ በደረቴ እያስዞረ በመቸብቸብ ለወያኔ አጎቶቹ ቅን ምርኮኛነቱን ያስመሰከረ ፤ የመጀመርያዉ "የደም ጽሁፍ ለገበያ" ወጣኒ ነበር ።

በጽናት ቆመዉ በጀግንነት የተሰዉትን የኢሕአፓ ታጋዮች ታሪክ ከደርግ የምርመራ ክፍል በተዘረፈ መረጃ እያስደገፈ ሲያስቸበችብ የከረመዉ የወያኔ አይጥ ዓላማዉ "የኢሕአፓን ሞት" በመለፈፍ "የኢሕአፓ ወራሾች ነን" ይሉ የነበሩትን አለቆቹን ማስደሰት ነበር ። ዛሬ ደግሞ የኮሎኔሉን "መጽሀፍ" አስጠግቶ በጻፈዉ ጽሁፍ "ኢሕአፓ ድሮ ቀረ" በሚል ያላዝናል ። አዲሱ ተልዕኮዉ ከሻቢያ ወፍነቱ ጋር የተቆራኘ ካልሆነ በቀር ያኔ ወያኔ ጉያ ተሸጉጦ ሳለ ያልተሳካለትን የመሞከሩ ፋይዳ ግልጽ አይደለም ። አበዉ ሲተርቱ "ልፋ ያለዉ በህልሙ ዳዉላ ይሸከማል" ይላሉ ። በዚህ ፈንታ ኮብላዩን ኮሎኔል ለመግደል ከዳንሂል መኖሪያዉ ስለተላኩት የሻቢያ ፈዳያን ቡድን ጉዳይ የሚያዉቀዉን እዉነት ከቅጥፈቱ ጋር ቀይጦም ቢሆን (የአቦይ ስብሃትን ምስክርነት አስመርኩዞ) ጫጭሮ በነበር ፤ በጥርጣሬ አሽቀንጥሮ ከወረወረዉ የየዋህን ማህበረሰብ ዕቅፍ ዉስጥ ተመልሶ ለመግባት በቻለ ።የደብረ ዘይቱ የሌት ወፍ አሳዛኝ ዋሾ ነዉ ። ይበልጥ በዋሸ ቁጥር ለወደፊቱ ሊጫጭርበት ቃል የሚገባበት ርዕሰ ጉዳይ ብዛትና ክብደት ይጨምራል ። ቁጭበሉነት ፤ ያዉም በዚህ ዘመን በቀላሉ የሚካኑት የማፍዘዣ ጥበብ ነዉ ብሎ ያደነቀረዉ ማን ይሆን?

እዉነቱን ለመናገር ፤ የሰዉ በላዉን ኮሎኔል "የደም መጽሀፍ" አራብቶ የመበተኑ ድርጊት የፈጠራ መብትን ለመጋፋት ወይም የሕትመት ነጻነትን ለማገድ የተወሰደ ርምጃ ከቶ እንዳልነበረ ለማሳዩት የደብረ ዘይቱን የሌት ወፍ ዋቢ ማሳለፍ ብቻዉን በቂ ነዉ ። ጉዳዩ ያ ቢሆን ኖሮ ከ"ማስታወሻ" እስከ "ቅብጥርሶ" ስንትና ስንት የባንዳ ቅርሻት የሕትመት ዉጤቶችን በኮንቴይነር ዱባይ ድረስ እያመላለሱ መሸቀጥ ባልቻለ ነበር ።ኮብላዩን ዐረመኔ ኮሎኔልና "ትግላቸዉ"ን በሚመለከት ብዙ ብዙ እየተባለ ነዉ ።

የአሳታሚዉን መልካም ሰዉነትና አዲሱን "የደም መጽሀፍ ፕሮጌ" በጨረታም ሆነ ያለጨረታ ለመረከብ እስኪበቃ ድረስ ያደረገዉን ጥረት ለመከላከያ በመዘርዘር የተጻፉ መሟገቻዎችም ለድህረ-ገጽ ንባብ በቅተዋል ።ይሁንና ያዘሉትን ፍሬ ከተጣደፉ መደምደሚያዎቻቸዉ ደብሎ በቅጡ ለመዘነ ሰዉ አንድም ከታማኝነት ወይም ከወዳጅነት ድጋፍ የመነጬ ፤ አንድም የስነ-አመክንዮ ችግር ያለባቸዉ በመሆኑ ዉሃ አለማንሳታቸዉ በግልጽ ይስተዋላል ።

ኮሎኔል መንግስቱንና ግብረአበሮቹን በሚመለከት የግፍ በደላቸዉ ቀጥተኛ ተቀባይ የሆነዉ ትዉልድ ይቅርና ተከታዩ ሳይቀር ከወዲሁ የሚጠጉበትን ከለላና የሚወረዉሩትን ቅዝምዝም ያዉቀዋል ብዬ አምናለሁ ። ልበ ደንጊያዉ ኮሎኔል "ትግላቸዉ"ን ለሕትመት እንዲያበቃ አልመዉ የሚችሉትን ሁሉ ያደረጉቱ በወንጀል ተባባሪ "ጓዶቹ " ከዛሬዉ ለሆሳሳቸዉ በስተያ የሰነቁልን ከቀድሞዉ ደም አዉርድ ዘመነ ሥልጣናቸዉ ያልተለዩ ዕልቂት መሆኑን እንገነዘበዋለን ። "ዴሞክራስያን" ሲዘምር ያለምትክ እንደወጣ ያስቀሩትን ትዉልድ ታክከዉ የሚያዘሩት ዕንባም ከልባቸዉ ያልፈለቀ ፤ ይልቁኑ ለበቀል አድፋጭ ቀን ጠባቂነታቸዉን የሚያሳይ ማስረጃ

ነዉ ። የትናንት ጭካኔ ግብራቸዉ ከዛሬዉ ጽድቅ ናፋቂነታቸዉ ጋር አለመሰናኘቱ በአባቶች ብሂል "ሰይጣን ሲያርም ባህታዊ ያስንቃል" ን ሊያስተርት ይበቃል።

ቅር ያሰኘኝን አንድ ወገን ሳልጠቅስ ፤ ይህንን ከሚገባዉ በላይ የረዘመ መጣጥፍ ልቋጨዉ አልሻም። ከአንድ አሥርት ዓመታት ትንሽ ቀደም ብሎ "መቃብር ቆፋሪዉና የሬሳ ሳጥን ሻጩ" የተሰኘዉ ተዉኔት በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ትወናና ዝግጅት(አምስት ኪሎ ይመስለኛል) ተመድርኮ አይቼዉ ወድጄዉም እንደነበር ከቶ አልረሳዉም ። ጸሐፌ-ተዉኔቱንማ በአድናቆት ሰማየ ሰማያት ነበር ያደረስኳቸዉ-" ደፋር... ጀግና" ብዬ ። ከዚያኔ አንስቶ እኚሁን ሰዉ (ታላቅ የሥነጽሁፍ ምሁርነታቸዉ ይታወስ ) በልቤ ሳከብራቸዉ ፤ ሙያቸዉንና ባህላችንን በተመለከተ የሰነዘሩትን አስተምህሮ በጽሁፍ ደረጃ አሳድጄ ተከታትያለሁ ። ከላይ በጠቀስኩት ቴያትር ሤራ ዉስጥ የሬሳ ሳጥንን ተመርኩዞ በምሬት ከምንስቅበት ጉዳዮች አንዱ "ቀይ ሽብር" ነዉ ። አንዱ ገጸ ባህሪ የሚያወርደዉ ቃለ-ተዉኔት - "ቀይ ሽብር ይፋፋም ፤ የሬሳ ሳጥን በርካሽ እንሸጣለን" የሚል ነበር መሰለኝ ባልሳሳት ። ይህንን እዉነት በይፋ ሳይፈራ የገለጸ ጸሐፌ ተዉኔት ወመምሕር ዛሬ ተመልሶ ለቀይ ሽብረኞቹ ፊታዉራሪ ጥብቅና ቆሞ ሲሟገት ያነበብኩ መሰለኝና ደነገጥኩ ።... "መቼም እንዳንተ አይነት ለዝናዉ ሙት የሆነ መቃብር ቆፋሪ አይቼም አላዉቅ ፤" ነበር የሚል የሬሳ ሳጥን ሻጩ ....

ጨረስኩ።